# ያገሬ ልጆች ምን ትላላችሁ? ኢጆሌ ቢያ ማል ጀተን ?!
# ትግሬና ትግሬ ወያኔን እንዴት እንለይ?

ሰርፀ ደስታ

**December 17, 2017 19:50**

እኔ ክስተቶችን በማስተዋል የምተነትን እንጂ የታሪክም የፖለቲካ ሰው አደለሁም፡፡ ጥረቴ ግን ብዙ ነገሮች በመቀባባትና በመላላስ ቀስ እያሉ አደጋ እየሆኑብን እንደመጡ ስለተረዳሁ በግልጽ መወገዝ አለበት ብዬ የማምነውን ማውገዝ ነው፡፡ አካፋን አካፋ ዶማን ዶማ ማለት ግድ እንደሆነ ይሰማኛል፡፡ ወያኔ ገዳይ ነው፡፡ ብዙ ትግሬዎች ግን የወያኔ ደጋፊዎች ናቸው፡፡ ኦነግ ገዳይ ነው! ምንም ጥርጥር የሌለው፡፡ ብዙ ኦሮሞ የኦነግ ደጋፊ ሆኖ ዛሬ ለገባበት ቀውስ እንደደረሰም አሁንም ያልተረዱ አሉ፡፡ ሌላም ሌላም፡፡ የውሸት እየተቀባባን እውነታውን ብንደብቀውም ይሄው ነቀርሳ ሆኖ እየፈጀን ነው፡፡ ወንጀለኞችን እያከበርን የአገርና ሕዝብ አሌኝታና ምልክት የሆኑን አዋርደናል፡፡ በመላላስ በመቀባባት የትም አንደርስም፡፡ አሁን ለብዙዎቻችን አንድ ነገር እየተገለጸ የመጣ መሰለኝ፡፡ የዘር ፖለቲካ ብዬ አላሳንሰውም፡፡ ጉዳዩ ከዛም በላይ እንደሆነ ይታያልና፡፡ ወያኔ ከመጀመሪያውም ዓላማ ያደረገችው ኢትዮጵያንና ለኢትዮጵያ ጠንካራ መሠረት ናቸው የምትላቸውን ሕዝቦችና ታሪኮችን ማውደም ከዛም ….. በአሁኑ ወቅት ትግሬንና ትግሬ ወያኔን መለየት እስኪሳን ድረስ ኢትዮጵያዊ ስሜት ያለው ትግሬ አጥተናል፡፡ ይህን ጉዳይ በብዙ መልኩ ልናስታምመውም ብንፈልግም ምን አልባት ተደብቀው ያሉ ኢትዮጵያዊ ትግሬ ይወጡ ይሆናል ብለን ብንጠብቅም በስም ከአወቅናቸው ጥቂቶቹ በቀር ዝር ያለ የለም፡፡ ነገሮች በገፉ ቁጥርም የሚመጣው አደጋ አስፈሪ ሊሆን ይችላል፡፡ ከጅምሩ ጀምሮ 27 ዓመት አማራ የተባለው ሕዝብ በተለያዩ ቦታዎች ሲታረድ ሲሳደድ ብዙም ትኩረት አልተሰጠውም፡፡ በሶማሌ ታጣቂዎች ኦሮሞ የተባለ ሁሉ እየደረሰበት ያለውን አረመኔያዊ ግፍ ስንሰማ ይሄው ብዙ ወራቶች አስቆጠርን፡፡ አሁን ደግሞ የኦሮሞው ግድያ(አረመኔያዊ)ና ለጆሮ የሚሰቀጥጡ ግፎች እንደቀጠሉ ይሄው ሶማሌ ደግሞ በሀረርጌ እያለቀ ነው፡፡ ሶማሌ ብቻም ሳይሆን አብሮ ተጨማሪ የኦሮሞ እልቂትም በእነዚሁ ቦታዎች እየሰማን ነው፡፡ ልብ በሉ በቀደም በጨለንቆ የወያኔ ሠራዊት ብዙ ሰዎችን መግደሉን፡፡ ዛሬ በምዕራብ ሀረርጌ የሆነው የሶማሌና ኦሮሞ እልቂትም ወያኔ በገዛቻቸው ቅጥረኞች እንደሆነ እያየን ነው፡፡ ይሄ ሊደረግ እንደታሰበ ቀደም ብለን እናውቅ ነበር፡፡ ጉዳዩንም እየተከታተሉ የነበሩ ለሕዝብ ቀድመው ይፋ አድርገውት ነበር፡፡ ከመጀመሪያውም የሶማሌ ታጣቂዎች በኦሮሞ ላይ የዘመቱበት አላማው ይሄ ነበር፡፡ ኦሮሞ በአጸፋው ደግሞ ሶማሌን እንዲፈጅና ወደለየለት የብሔር ጦርነት ለማሳደግ፡፡ ሆኖም የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት የወያኔ ሴራ ስለገባው በአጸፋ በአንድም ኦሮሚያ ውስጥ በሚኖር ሱማሌ ላይ ምንም አይነት ችግር እንደይገጥመው ሕዝቡን በማንቃት ወያኔ ያሰበችውን ጥፋት እንዳይሳካላት አድርጎት ነበር፡፡ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት በዚህ ወቅት ያሳየው ጥረት ብዙ ነው፡፡ ኦሮሞ ሁሉ ከሶማሌ እየተለቀመ ይውጣ በተባለበት በዛው ሳምንት ሶስተ ቀን ባልሞላ ነበር የኦሮሚያ ክልላው መንግስት ባለሙያዎቹን በአካል በተለያዩ ቦታዎች ተንቀሳቅሰው ሕዝቡ የተሸረበውን ሴራ ተረድቶ ምንም አይነት ችግር በሱማሌ ተዋላጆች ላይ እንዳይደርስ፡፡ ምንአልባትም ቅጥረኞች ችግር እንዳይፈጥሩበት ሕዝቡ ለሱማሌ ተወላጆች በተለየ ጥበቃ እንዲያደርግላቸው ያስተባበረው፡፡ ዛሬ ያ ያልተሳካላት ወያኔ እንደተነገረውም ዛሬ በምዕራብ ሀረርጌ በፖሊስ ጥበቃ ሲደረግላቸው ነበር በተባሉ (ወያኔ ነች ያለችው) የሱማሌ ተወላጆች ላይ በቅጥረኞቿ እልቂት ፈጽማለች፡፡ ይህ ያደረገችው ኦሮሞ ሶማሌን ገደለ ለማለት ብቻም ሳይሆን በፖሊስ ጥበቃ ሲደረግላቸው የነበሩ በማለት በኦሮሚያ ፖሊስ ላይ ጥርጥር እንዲኖር ለማድረግ በምትኩም ሰው በላ ኢጋዚ ወያኔን በይፋ ለማሰማራት እንደሚቻት እንደሆነ አስተውሉ፡፡ በጨለንቆ ወያኔ በቅሊቦቿ ኢጋዚ የፈጸመችውን እልቂት የኦሮሚያ ክልል ማውገዙንና በግልጽ ጉዳዩን ወንጀለኛ ሲል መኮነኑ ይታወሳል፡፡ አስቀድሞ በኢሊ አባቦራ የትግራይ ተወላጅ የሆነ የደህንነት አባል የኦነግን ባንዲራና በኦሮሚኛ የተጻፉ የተለያዩ ሕዝብን በሕዝብ የሚያነሳሱ ጽሁፎች ሲያሰራጭ መያዙ ይታወሳል፡፡ በተለያዩ ቦታዎችም የትግራይ ተወላጆች በአሁኑ ወቅት ልዩ ጥበቃ እየተደረገላቸው በዚሁ ተግባር መሰማራታቸው እየታየ ነው፡፡ በዚህ መልኩ የት ድረስ እንደሚሄዱ ባይገባኝም የሆነ ቦታ ሲደርስ ግን ትግሬ የተባለ ሁሉ የኢትዮጵያና ሕዝቦቿ ጠላት ነው የሚለው ግልጽ አቋም ሊመጣ እንደሚችል

እሰጋለሁ፡፡ ወያኔ ማለት ትግሬ ትግሬ ማለት ወያኔ ነው የሚለው አባባል እገዘፈ እየመጣ ነው፡፡ የኢትዮጵያውያንም ሰቆቃ በዝቶ በፈሰሰበት በዚህ ወቅት እኳን ትግሬ የተባለ በአብዛኛው ምን አልባትም ጥቂት ብቻ ከሚባሉት በቀር ወያኔነቱን እያሰመሰከረ ነው፡፡ የከት ሆነው ለረዥም ዘመናት ተደብቀው የኖሩትም ይሄው ዛሬ ይፋ ሆነው ወያኔነታቸውን እያነበብን ነው፡፡ እኔ አሁንም ቢሆን ከትግራይ ውጭ ያለውን ትግሬ እንጂ ትግራይ ውስጥ ያለው ትግሬ ብዙ ወያኔን የማይደግፍ አለ የሚል እምነት አለኝ፡፡ ብዙዎች በዚህ ጉዳይ አይሰማሙም፡፡ ትግሬ ወያኔ ወያኔ ትግሬ የሚለው እያየለ መጥቷል፡፡ በእርግጥም ወያኔ የምትፈልገው ይሄንኑ ነው፡፡

በእርግጥም አሁን ባለው ትግሬ ኢትዮጵያዊ ትግሬ ለመኖሩ ጥርጣሬ ለመፈጠሩ ታሪካዊ ሂደቶችም ምልክት ሰጭ ናቸው፡፡ ከወያኔ ታሪክ እንደምንረዳው ኢትዮጵያዊ የነበሩ ትግሬዎችን ሁሉ ያለ ርህራሄ እንደፈጀችና አሁን ላይ ራሳቸውን ደብቀው ከተረፉ ጥቂት በቀር ሌላው ትግሬ የወያኔ ወላጆች ትግሬ ያፈሯቸው ናቸው፡፡ የወያኔ ወላጆች ደግሞ ባንዳዎች አንደነበሩና በግልጽም በኢትዮጵያ ሀፍረቷን በተከናነበቸው ጣሊያን ይረዱ እደነበር እናያለን፡፡ ዛሬ የወያኔ ዋና ሆኖ የተሾመው ደብረጺዮን የሚባለው ግለሰብ እንደምሳሌ ልዩ ስልጠና የተሰጠው በጣሊያን ነው፡፡ በአጠቃላይ አማራን ማጥፋት የሚል ማኒፌስቶ የጻፈቸው ወያኔ መስራቾቿ የኢጣሊያን ባንዳ ልጆች አባቶቻቸው በኢትዮጵያ ጀግኖች የተፈጸመባቸውን ሀፍረት ለመበቀል ነበር፡፡ አማራ ያሉት ጣሊያን አማራና ኦርቶዶክስ ትል ስለነበር አባቶቻቸው የነገሯቸውን ነው፡፡ ማኒፌስቶው ግን ኢትዮጵያዊ የሆነን ሁሉ ማለት ነው፡፡ ትግሬ ኢትዮጵያውያን የወያኔ ተቀዳሚ ሰለባ ሆነው በ 17 ዓመት እማኝ በሌለበት እንዲያልቁ በመደረጉ ትግራይ ከኢትዮጵያዊ የጸዳ ክልል አደርገውታል ማለት ይሻላል፡፡ ባዶ 6 የተባለው ቡድናቸው 17 ዓመት ከዚያም በኋላ ጥቂት የተረፉ ትግሬ ኢትዮጵያውያነን መንጥሮ ጨረሷል፡፡ የወያኔ ተዋጊዎች ሊላው ክልል ሲገቡ ኢትዮጵያ ጠላታችን እያሉ እንደገቡ አስታውሱ፡፡ ይሄ ከልጅነታቸው ጀምሮ ሲነገሩት ያደጉት ነበር፡፡ እንግዲህ በትግራይ የሚኖረውን ትግሬ እስኪ እንየው በሌላ ቦታ ከሚኖረው ትግሬ ጋር አናመሳስለው ብንልም ዛሬ ያለው በትግራይ የሚኖረው ትግሬም ኢትዮጵያዊ ከቀረው በጣም የሳሳ እንደሚሆን እናስባለን፡፡ ኢትዮጵያዊ ትግሬ ያለ እማኝ ወያኔ የዘር ማጥፋት ፈጽማበታለች፡፡ ሌላው አማራ በሉት ኦሮሞ ቢገደልም ቢያንስ ወሬው ተሰምቷል፡፡ የ 17 ዓመቱን የ ባዶ 6 እና ከዛም በኋላ እየታደነ ያለቀውን ኢትዮጵያዊ ትግሬ ለወሬም ምልክት ሳይኖር ነበር፡፡

ከሞላ ጎደል ከላይ የጠቆምኩት አሁን ያለውን ትግሬ ስብጥር የሚጠቁም ነው፡፡ ወያኔ ትግሬና ኢትዮጵያዊ ትግሬ፡፡ እነ ወዲ ሻምበልና ጥላሁን ስንት ኢትዮጵያዊ ትግሬ እንዳላቸው አናውቅም፡፡ እዚህ ላይ የግለሰቦቹን ሥም ማንሳት የፈለኩት ኢትዮጵያዊ ትግሬ ከምናውቀው የትግሬ ሕዝብ እነሱን በማየቴ ነው፡፡ በቅርብ እንደ ጓደኛ ብቻም ሳይሆን እንደወንድም እንተያየለን ብለን በአመናቸው ትግሬዎች የተካድን ሥንት እንደሆንን አላውቅም፡፡ ድሮ እንደምንሰማው ትግሬ ሀይማኖተኛ ነው ነበር፡፡ ሐይማኖተኛ ትግሬ የገጠመን ግን ሥንቶቻችን እንሆን፡፡ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች በወያኔ ማኒፌስቶ ኢላማ ከሆኑት ስለሆኑ አይደንቅም፡፡ ከላይ ሥሙን የጠቀስኩት ጥላሁን የሚነግረን ሚስጢር ጉዳዩ ከኦርቶዶክስነት ጋር ባቻ አደለም በተመሳሳይ የእስልምና ተከታዮችም ኢላማ ነበሩ፡፡ አላማው ደግሞ እምነት ከአለ አገር ወዳድነት፡፡ ለሕዝብ አሳቢነት አለና ወያኔ ከቆመችለነት የአገርና ሕዝብን ማጥፋት አላማ ስለሚያደናቀፋት እነዚህን እምነቶች ኢላማ ማድረግ ግድ ነበረባት፡፡ ዛሬ የምናየው ትግሬ እስላምም ኦርቶዶክስም ነኝ ሊል ጳጳስ ሼክ ሊሆን ይችላል፡፡ አውን ግን ነው ብለን ስናስብ አስደንጋጭ እውነታዎችን እናያለን፡፡

እንግዲህ ትግሬ ወያኔዎች በአገርና ሕዝብ ማጥፋት ላይ ዓላማ አድርገው መነሳታቸው ግልጽ ነው፡፡ ከተለያየ ሕዝብም በገንዘብና በተለያየ ጥቅማጥቀም የቀጠሩብን ብዙ ናቸው፡፡ ተቀጣሪዎቹን በማስጠንቀቅም አስፈላጊውን ምክርም በመስጠት ወደልቦናቸው መመለስ ይቻላል፡፡ አብዛኞቹም ለጥቅም ብለው እንጂ የአመኑበትን እያደረጉ ስላልሆን፡፡ አላማዬ ብሎ በኢትዮጵያውያን ሁሉ ላይ የተነሳውን የትግሬ ወያኔን መረብ ግን መበጣጠስ እንዴት ይቻላል ነው ጥያቄው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም የቀሩንን ትግሬ ኢትዮጵያያውያንን ከትግሬ ወያኔ እንዴት እንለይ የሚለው ይነሳል፡፡ ከዚህ በኋላ ትግሬ የሚመራው ሠራዊት የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ነው ብሎ ማሰብ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የታጠቀ አሸባሪን የፈለገውን እንዲያርድ መፍቀድ ነው፡፡ አሁን ኢትዮጵያ ያላት የትግሬ ወያኔ አሸባሪ ጦር እንጂ የኢትዮጵያ መከላከያ አደለም፡፡ ከዚህ በኋላ አጥብቀን ልንሰራበት የሚገባው በዚሁ የሽብር ጦር ውስጥ የሚያገለግሉ የሌላ ሕዝብ ተወላጆች ሚናቸውን ለይተው እንዲሰለፉ ነው፡፡ ከዚህ በኋላ ትግሬ ወያኔ የሚያስተዳድረውን ማንኛውም ተቋም የሽብር ማስፈጸሚያ አካል እንደሆነ ማስብ ነው፡፡ ለምሳሌ ዜጎችና ፓስፖርት ተቋማት፣ በየማጎሪያቤቶች፡፡ በየ አውሮፕላን ማረፊያው የሚቀበሉት ትግሬ ወያኔዎች በአገራችን መብት እንደሌላቸው ተረድተን ግዜ ሳንሰጥ ከእነዚህ አካባቢዎች ማጽዳት ነው፡፡ የበአዴንና ኦህዴድ

ድርጅቶችም ከሕዝብ ጎን ነን ከአሉ ይሄንኑ እና የመሰሉ ሂደቶችን በይፋ መጀመር አለባቸው፡፡ በግልጽም እነዚህ ቦታዎች ሙሉ በሙሉ በሌሎች ኢትዮጵያውያን በአስቸኳይ እንዲተኩ ግድ ይላል፡፡ ከዚህ በኋላ ትግሬ እያየ ደሙ የሚፈላን ሕዝብ ትግሬዎች ሊያስተናግዱት አይችሉም፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ትግሬ ወያኔዎችና ቅጥረኛ አጋሮቻቸው በየቦታው በሕዝቦች መካከልና በተለያየ ቦታ እየፈጸሙት ያለውን ሴራና አረመኔያዊ ድርጊት ለመቀልበስ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ራሱን ወያኔ ከሰራችለት የብሔር ጉሮኖ ውስጥ አውጥቶ በአንድነት በትግሬ ወያኔ ላይ ሊነሳ ይገባል፡፡ ዛሬ የተገደለው ሶማሌ በሶማሌነቱ ነው፡፡ እየተገደለ ያለው ኦሮሞ በኦሮሞነቱ ነው ሲገደል የኖረው አማራ በአማራነቱ ነው፡፡ ክልል ጥር ኢትዮጵያዊ አልነበረውም፡፡ በማንነቱ ማንም ነክቶት አይታወቅም፡፡ በፈለገበት ቦታ እንደተቀላቀለው ሕዝብ አብሮ ይኖር ነበር፡፡ ወያኔና ኦነግ ያጠሩብንን አጥር ሰብረን መውጣት ግድ ይለናል፡፡ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ለመታደግ ራሳችንን ከእነዚህ የዘር ማንነት ቀለበት እናውጣ፡፡ እኔ እንደሌላው መጀምሪያ ሰው ነኝ እያልኩ እጅግ ላርቀው አልፈልግም፡፡ በቃ እኛ ኢትዮጵያዊ ነን፡፡ በእርግጥም በነገድ አንድ የሆንን የተለያየ ቋንቋና ባህል ያለን ነን፡፡ በቅርቡ ሳይንስ ስለኛ ያጠናውን የዘር ማንነት ከዚህ በፊት እንዳጋራኋችሁ የምታስታውሱ ትኖራላችሁ፡፡ ኩሽ ሴም የሚባል ነገር በደማችን የለም፡፡ ኩሽና ሴም ተብለው የተሰየሙትን ቋንቋዎች የሚናገሩ ኢትዮጵያውያን ሁሉ በሚያስገርም ሁኔታ አንድ ዘር የሆኑ ከ 3 ታላላቅ ነገዶች ውሕደት የመጡ ናቸው፡፡ ከ 40-60 በመቶ የሚሆነው ዘር ከጥንታዊው ሌቫንት ከሚባለው የተወሰደ ሲሆን ቀሪው ኢትዮጵያዊው አሪና ሌላ መሠረቱ ለጊዜው ያልታወቀ ግን ኢትዮጵያውያኖችና የኬኒያው ማሳይ ሕዝቦች በብዛት የሚጋሩት ዘር ነው፡፡ እኛ በተለይ ኩሽና ሴም ተናጋሪ ናቸው የተባሉት ፍጹም የማይለያይ ዘር ሲኖራቸው ግን ከሌሎች አፍሪካ ወገኖች የምንጋራው ዘር ከአለም በጣም አነስተኛ ነው፡፡ የእኛ መዋቅሮች ከላይ የጠቆምኩዋችሁ 3 የዘር መሠረቶች ናቸው፡፡ ወያኔ ትግሬ እንደፈጠረችልህ ሳይሆን አማራ፣ ኦሮሞ፣ ሶማሌ፣ ትግሬ፣ አፋር፣ … የአንድ አያት ልጆች ናቸው፡፡ አገራቸውም የሀበሻ ምድር ኢትዮጵያ ነች፡፡ አማራ ሀበሻ ከተባለ ሶማሌም ኦሮሞም፣ አፋርም ሀበሻ ነው፡፡ ይህ ነው አውነታው፡፡ ዛሬ የተገደለው ሶማሊኛ ተናጋሪ ወገንህ እንጂ ሱማሌ ብለህ የምታስበው የተለየ ዘር አደለም፡፡ ሁላችንም ማንነታችንን የሰነጣጠቁንንና እየገደሉን ያሉትን ትግሬ ወያኔዎችን በጋራ እንዋጋቸው፡፡

እግዚአብሔር ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይታደግ! አሜን!

ሰርፀ ደስታ